ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)

www.KINIJIT.org

# የአዲስ አበባ ከተማ የአስሩ ክፍለ ከተሞች የቅንጅት ተወካዮች

# የአቋም መግለጫ

እኛ በአዲስ አበባ ከተማና በዙሪያው የምንገኝ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የክፍለ ከተማና የቀበሌ አመራር አባላት ጥር 25/2000 ዓ.ም በቅንጅት ጽ/ቤት አዳራሽ ባደረግነው ስብሰባ በጥቂት የፓርቲያችን ከፍተኛ አመራር መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት በጥልቀት ተወያይተንበታል፡፡ በውይይታችንም ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ በግንባር ቀደምትነት ጥቂት ተከታዮችን አስከትለው ፓርቲያችንን የመከፋፈል አድማ እያካሄዱ መሆኑን የተለያዩ ማስረጃዎችን በማቅረብ ተነጋግረንበታል፡፡ እነዚህ ከፋፋዮች በአሁኑ ጊዜ እየተከተሉ ያሉት መንገድ በሃሳብ ልዩነት ላይ የተመሰረተ ገንቢ ትግል ሳይሆን በአቋም ልዩነት ላይ የተመሠረተና ሕዝብ ያመነበትንና ሕይወቱን የሰጠበትን ወደፊትም በሕዝብ ሠላማዊ ትግል ውስጥ ግንባር ቀደም አታጋይ ይሆነኛል ብሎ በሙሉ ተስፋ የሚከተለውን ቅንጅትን የማፍረስ ተግባር እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ከፋፋዮች ሕዝብ በሰላማዊ ትግሉ ላይ እምነት እንዲያጣ፣ ከኢሕአዴግ አመራር ውጭ ጠንካራ ፓርቲ እንዳይኖር ለማድረግ እና ፓርቲያችን ቅንጅት ተንበርካኪ እንዲሆን አቅደው እንደተነሱ ከተግባራቸው አረጋግጠናል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ በእነዚህ ቅንጅትን የማፈራረስ ተልዕኮ ባላቸው አንጃዎች እንዳይወናበድና የአንጃዎቹ አፍራሽ እንቅስቃሴም በእንጭጩ እንዲቀጭ በማድረግ ረገድ የበኩላችንን ድርሻ መወጣት እንዳለብን አምነናል፡፡ ስለዚህ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎቻችን በሙሉ ዛሬም እንደትላንት ከጐናችን ቆማችሁ ከውስጣችን ሆነው ሊያዳክሙን የተነሱትን እኩያን በጋራ እንድንታገል ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡ በዚህ እንቅስቃሴያችንም በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል አመራር ቅንጅት በሙሉ እግሩ እንዲቆም ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በጽናት እናምናለን፡፡ ለዚህም የሚከተለውን አቋም ወስደናል፡፡

1. የተጓደሉ የላዕላይ ምክር ቤት አባላትን መርጦ የማሟላት ሥልጣን የጠቅላላ ጉባኤው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የሚመራው አንጃ የላዕላይ ምክር ቤት አባላትን በራሱ በማሟላት በቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ስም ለመንቀሳቀስ የሚያስችለው የማጭበርበሪያ ካባ ለመደረብ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ድርጊቱ ሕገ ወጥ መሆኑን ሕዝቡ እንዲያውቅና ድርጊቱም የሕዝብ ፓርቲ የሆነውን

ቅንጅትን ለማፍረስ የሌላ ኃይል ተልዕኮ ለማሟላት የአንጃ ቡድን የሚያካሂደው እንቅስቃሴ መሆኑን እንዲገነዘብ እናሳስባለን። ስለሆነም በአስቸኳይ የቅንጅት ጠቅላላ ጉባኤ ከመላው ኢትዮጵያ የክልል ዞኖችና ወረዳዎች ተጠርቶ በፓርቲው ቀጣይ ሕልውና ላይ መፍትሔ እንዲሰጥ እንጠይቃለን።

2. በወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳና በአቶ ግዛቸው ሽፈራው ጥምረት በአፍራሽነት እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ቡድን በቅንጅት ጽ/ቤት ከሚሠሩ የአመራር አባላት ጋር ተገናኝቶ ችግሩን በውይይት ለመፍታትና እንደቀድሞው አንድ ሆኖ ለመቀጠል የሚፈልግ በማስመሰል የአስታራቂ ሽማግሌዎችን የእርቅ ሂደት የሚደግፍና በሂደቱም ውስጥ የተሳተፈ መሆኑን ያሳያል። በውጭ ደግሞ ያለ ሥልጣኑ የላዕላይ ምክር ቤት የማሟያ ስብሰባ በመጥራት ሕገ ወጥ ስብሰባ በማድረግ ላይ ይገኛል። እነዚህ አፈንጋጮች አዲስ ቅንጅት በማቋቋም ሕዝቡን ለማወናበድ ከሚጥሩ ከእነ አቶ ተመስገን ዘውዴ ጋር አፍራሽ አድማቸውን ቀጥለዋል። እነ አቶ ተመስገን ዘውዴ የቅንጅት መሪዎች ከእስር ከመለቀቃቸው በፊት ቅንጅትን ለማፍረስ እቅድ አውጥተው በ1500 ሰዎች የተፈረመ ሰነድ በማቅረብ አዲስ ፓርቲ አቋቁመዋል። ስለዚህ ከእነዚህ አፍራሽ ኃይሎች ጋር በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንቅስቃሴያቸውን ለማዳመቅ የሚተባበሩ ሁሉ እንዲታቀቡ እናሳስባለን።

3. በቅርቡ ለሚጠራው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አዘጋጅነት ለተመረጡ ኮሚቴዎች ሙሉ ድጋፋችንን በመስጠት ጠቅላላ ጉባኤው በተሳካ ውጤት እንዲጠናቀቅና ለቅንጅት ዳግም ትንሳኤ ሰላማዊ ትግሉ የሚጠይቀውን ሁሉ ለመክፈል መዘጋጀታችንን እናረጋግጣለን።

ቅንጅት አንድ ነው!